# የኩፍኝ በሽታ

## ኩፍኝ ከባድ በሽታ ነው



ኩፍኝ የቆዳ ሽፍታ እና ከፍተኛ ራስ ምታትን የሚያስከትል ከባድ በሽታ ነው።

ኩፍኝ በፍጥነት የሚተላለፍ በሽታ ነው። በሽታው የሚሰራጨው በኩፍኝ የተያዘ ሰው ሲተነፍስ፣ ሲያስለው ወይም ሲያስነጥስ ነው።

ክትባት ያልወሰደ ሰው ለበሽታው ተጋላጭ ከሆነ
በኩፍኝ የመያዝ ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

የኩፍኝ በሽታ በተለይ ለጨቅላ ሕጻናትና አፍላ ልጆች አደገኛ ሊሆን ይችላል። አልፎ አልፎም ሞት ሊያስከትል ይችላል።

## ቤተሰብዎን ከኩፍኝ ይጠብቁ



ቤተሰብዎን ከኩፍኝ ለመጠበቅ የተሻለው መንገድ ክትባት መውሰድ ነው። ሐኪሞች ሁሉም ሕጻናት የ MMR ክትባት እንዲወስዱና አዋቂዎችም ክትባቱን በልጅነታቸው ካልወሰዱ እንዲከተቡ ይመክራሉ።

የ MMR ክትባት የኩፍኝ በሽታን በመከላከል ረገድ ጉዳት የማያስከትል እና ውጤታማ ነው። ጆሮ ደግፍና ሩቤላንም ይከላከላል።

የ MMR ክትባትን መውሰድ በኩፍኝ ከመያዝ በእጅጉ ይሻላል።

ሕጻናት አብዛኛውን ጊዜ በክትባቱ ምክንያት የሚያጋጥማቸው የጎንዮሽ ጉዳት የለም። ጥቂቶቹ እንደ ትኩሳት፣ መጠነኛ ሽፍታ ወይም ቁስለት የመሳሰሉ የጎንዮሽ ጉዳት የሚያጋጥማቸው ሲሆን፣ እነዚህም ቢሆኑ መጠነኛ እና ብዙ የሚቆዩ አይደሉም።

## የ MMR ክትባት ኦቲዝም አያስከትልም

ሳይንቲስቶች አንድ ሕፃን በኦቲዝም እንዲጠቃ ሊያደርጉ የሚችሉ መንስኤዎችን በማጥናት ላይ ናቸው። አብዛኞዎቹ ሳይንቲስቶች አንድ ሰው በቤተሰብ የዘር ውርስ ሳቢያ ኦቲዝም ሊያዳብር እንደሚችል ይስማማሉ። በኦቲዝም እና ግለሰቡ በሚኖርበት አካባቢ መካከል ሊኖር የሚችለውን ቁርኝትንም በማጥናት ላይ ናቸው።

የትኞቹም ጥናቶች በኦቲዝም እና በMMR ክትባት መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት አላገኙም። ይህ በዓለም ዙሪያ ባሉ ዶክተሮች እና ሳይንቲስቶች በጥንቃቄ ተጠንቷል።

ስለ ኩፍኝ በሽታ እና የMMR ክትባት ሌሎች ጥያቄዎች ካሉዎት ሐኪምዎን ይጠይቁ።

**ለተጨማሪ መረጃ፦**

www.doh.wa.gov/measles
www.kingcounty.gov/health/measles

Somali Health Board – Peace, Unity, Life, Health
Public Health – Seattle & King County
Washington State Department of Health

# በኩፍኝ በሽታ ተይዣለሁ ብለው ካሰቡ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

**የኩፍኝ በሽታ ምልክቶች እና የስርጭቱ ሁኔታ**

አብዛኛውን ጊዜ የኩፍኝ በሽታ የሚጀምረው በከፍተኛ ራስ ምታት፣ ማሳል፣ የሚፈስ ንፍጥ፣ እንዲሁም በቀሉ እና ውሃ ባዘሉ ዓይኖች ነው። ከ3-5 ቀናት በኋላ፣ የቆዳ ሽፍታ ከፊት በመጀመር ወደ ሌሎች የሰውነት አካላት ይሰራጫል።

በበሽታው ከተያዘ 4 ቀናት ብቻ ሆኖት ገና የቆዳ ሽፍታ ካልታየበት እንዲሁም ሽፍታው ከታየ 4 ቀናት ገደማ ከሆነው ሕመምተኛ የኩፍኝ በሽታ ሊተላለፍብዎ ይችላል።

የኩፍኝ ሕመምተኛው በቆየበት ክፍል ውስጥ በመቆየትዎ ብቻ በኩፍኝ በሽታ ሊያዙ ይችላሉ። የ ኩፍኝ በሽታ ቫይረስ ሕመምተኛው ክፍሉን ከለቀቀ በኋላ እስከ ሁለት ሰዓታት በአየር ውስጥ ይቆያል።

**ምልክቶችን ካስተዋሉ ውዲያውኑ ለሐኪምዎ ወይም ለጤና ተቋም ይደውሉ**

ለምርመራ መምጣት እንዳለብዎት ሐኪምዎ ወይም የጤና ተቋሙ ያሳውቅዎታል።

ኩፍኝ ተላላፊ በሽታ በመሆኑ በእንግዶች መቆያ ክፍል ውስጥ ለሌላ ሰው ሊያስተላልፉት ይችላሉ። ወደ ሕክምና ከመሄድዎ **በፊት** የኩፍኝ በሽታ ምልክቶች እንዳሉበዎት ለሐኪምዎ ወይም ለጤና ተቋምዎ መንገር አለብዎት። የኩፍኝ በሽታን እንዳያሰራጩ ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለብዎት መመሪያዎች ይሰጡዎታል።

**በኩፍኝ በሽታ ከተያዙ በቤትዎ ይቆዩ**

የኩፍኝ በሽታን ለሌሎች ማስተላለፍ የለብዎትም።

በኩፍኝ በሽታ ከተያዙ በቤትዎ ይቆዩ። ወደ ትምህርት ቤት፣ ስራ ቦታ፣ ወይም ወደ ሌሎች ሰዎች ቤት አይሂዱ።

እርስዎ ወይም የእርስዎ ልጅ ራስ ምታት እና የቆዳ ሽፍታ ካለባችሁ ታማሚ ጠያቂዎችን ወደ ቤትዎ አያስገቡ።

**ለተጨማሪ መረጃ:-**

www.doh.wa.gov/measles

www.kingcounty.gov/health/measles

DOH 348-651, July 2018 Amharic

Public Health
Seattle & King County

ይህ ሰነድ ለአካል ጉዳተኞች በሌሎች ቅርጸቶች ተዘጋጅቶ አለ። ጥያቄ ለማቅረብ፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 1-800-525-0127 (TTY/TDD 1-800-833-6388) ይደውሉ።